ይህ ማለት መምህራኑ ለጀማሪ መምህር የሥራ መደብ የተፈቀደውን መነሻ ደመወዝ እያገኙ የሚቆዩ ይሆናል።

1.5 በተለያዩ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ተደልድለው የማስተማር ሙያ ስልጠና (PGDT) ከጀመሩ በኋላ በአለም አቀፍ ብሎም በሀገራችን በተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሺኝ እንደዚሁም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ግጭት ምክንያት ማጠናቀቅ ያልቻሉ ሁሉም የአፕላይድ ሳይንስ ተመራቂ መምህራን የአገልግሎት ጊዜያቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ ለአንድ ጊዜ ብቻ የደረጃ ዕድገት የተፈቀደ ሲሆን ይኸውም፡-

1.5.1 ከ3 ዓመት በታች አገልግሎት ያላቸው ለጀማሪ መምህር የሥራ መደብ የተያዘው መነሻ ደመወዝ ያገኛሉ።

1.5.2 ከ3 እስከ 5 ዓመት አገልግሎት ያላቸው "መለስተኛ መምህር" ለሚለው ደረጃ የተያዘው መነሻ ደመወዝ ያገኛሉ።

1.5.3 ከ6 እስከ 8 ዓመት አገልግሎት ያላቸውና በማስተማር ስራ ላይ ያሉ የአፕላይድ ሳይንስ ተመራቂዎች ደግሞ "መምህር" ለሚለው እርከን የተያዘው መነሻ ደመወዝ ያገኛሉ።

2 የትምህርት ዝግጅታቸውን ከዲፕሎማ ወደ መጀመሪያ ዲግሪ ለማሻሻል በመንግስት ስፖንሰር አድራጊነት ስልጠና እየተከታተሉ ያሉ ነባር መምህራን፡-

2.1 በ2007ዓ.ም እና በ2008ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ተሰጥቷቸው ስልጠናውን እየተከታተሉ ያሉ ነባር መምህራን በሀገራችን በተከሰተው ኮቪድ 19 ወረርሺኝ እንዲሁም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው የጸጥታ ችግር ምክኒያት የማስተማር ሙያ ስልጠና ማጠናቀቅ አለመቻላቸው ይታወቃል። ስለሆነም በ2012ዓ.ም እና በ2013ዓ.ም በቅደም ተከተል የማስተማር ሙያ ስልጠና ማጠናቀቅ የነበረባቸው መምህራን ስልጠናውን ባያጠናቅቁም የአካዳሚክ ኮርስ ስለማጠናቀቃቸው ስልጠና ከሚወስዱበት ዩኒቨርስቲ ማስረጃ ካቀረቡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ትይዩ የደረጃ እድገት ያገኛሉ።

2.2 በ2012ዓ.ም እና በ2013ዓ.ም የባከኑ የትምህርት ጊዜያትን ለማካከስ በተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች የማስተማር ሙያ ስልጠና (PGDT) ማጠናቀቂያ ጊዜ ወደ 2014ዓ.ም እና 2015ዓ.ም የክረምት ወቅት ማሸጋሸግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።